# ምዕራፍ ሦስት

## የአብ ሥጦታ ለክርስቲያኖች (ለሰው ልጆች)

### ሀ. ልጁን ሰጥቶናል፤

"በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘለዓለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወድዷልና" (ዮሐ 3፥16) ብሎ ቅዱስ ዮሐንስ እንደተናገረ ጸጋ፣ ጽድቅ ወልድን ሕይወት እንዲሆነን ሰጥቶናል።

### ለ. ከልጁ ጋር ሁሉን ሰጥቶናል፤

"ለገዛ ልጁ ያልራራለት ነገር ግን ስለሁላችን አሣልፎ የሰጠው ያው ከእርሱ ጋር ደግሞ ሁሉን ነገር እንዲያው እንዴት አይሰጠንም።" (ሮሜ 8፥32) ብሎ ቅ.ጳውሎስ እንዳስተማረን።

### ሐ. መንፈስ ቅዱስን ሰጥቶናል፤

"... በሰማይ ያለው አባት ለሚለምኑት እንዴት አብልጦ መንፈስ ቅዱስን ይሰጣቸው?" (ሉቃ. 11፥13)

"ልጆችም ስለሆናችሁ እግዚአብሔር አባ አባት ብሎ የሚጮህ የልጁን መንፈስ በልባችሁ ውስጥ ላከ።" (ገላ 4፥6, 2ጢሞ 1፥7) ተብሎ እንደተነገረ።



### መ. ሥልጣን ሰጥቶናል፤

- የልጅነት ሥልጣን "ለተቀበሉት ሁሉ ግን በስሙ ለሚያምኑት ለእነርሱ የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ሥልጣንን ሰጣቸው።" (ዮሐ 1፥12) "የእግዚአብሔር ልጆች ተብለን ልንጠራ አብ እንዴት ያለውን ፍቅር እንደሰጠን እዩ እንዲሁም ነን" (ዮሐ 3፥1) ተብሏልና። በተጨማሪ
- በጠላት ላይ ሥልጣንን ሰጠን (ሉቃ 10፥19)

### ሠ. የዘለዓለም ሕይወትን ሰጥቶናል፤

"የእግዚአብሔር የጸጋ ሥጦታ ግን በክርስቶስ ኢየሱስ በጌታችን የዘለዓለም ሕይወት ነው።" (ሮሜ 6፥23)

"ከወደደን ከትልቅ ፍቅሩ የተነሳ በበደላችን ሙታን እንኳ በሆንን ጊዜ ከክርስቶስ ጋር ሕይወትን ሰጠን" (ኤፌ 2፥5, 1ዮሐ 5፥11) መጽሐፍ እንዳለ።

### ረ. መንግሥቱን ሰጥቶናል፤

"አንተ ታናሽ መንጋ መንግሥትን ሊሰጣችሁ የአባታችሁ በጎ ፈቃድ ነውና አትፍሩ።" (ሉቃ 12፥32) ብሎ ጌታችን እንደተናገረ።

## የአብ ፍቅር ለሰው ልጆች

### 1. እንዲሁ ወደደን፤

"በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘለዓለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን ሁሉ እንዲሁ ወድዷልና።" (ዮሐ 3፥16) በማለት ቅዱስ ዮሐንስ እንዳበሠረን።

2. ***ልጅን በወደደበት መጠን ወደደን፤***

"እንዲሁም ዓለም አንተ እንደላክኸኝ በወደድኸኝም መጠን እነርሱን እንደወደድሃቸው ያውቃል።" (ዮሐ 17፥23) እንዳለ መድኃኒታችን።

3. ***በዘለዓለማዊ ፍቅሩ ወደደን፤***

"እግዚአብሔርም ከሩቅ ተገለጠልኝ እንዲህም አለኝ በዘለዓለም ፍቅር ወድጀሻለሁ።" (ኤር 31፥3) ብሎ እግዚአብሔር በነቢዩ እንደተናገረ።

4. ***በገዛ ፈቃዱ ወደደን፤***

"በገዛ ፈቃዴ እወድዳቸዋለሁ" (ሆሴዕ 14፥4) ብሎ በሆሴዕ እንደተናገረ።

5. ***እኛ ሳንወድደው ወደደን፤***

"በዚህ የእግዚአብሔር ፍቅር በእኛ ዘንድ ተገለጠ። በእርሱ በኩል በሕይወት እንኖር ዘንድ እግዚአብሔር አንድ ልጁን ወደ ዓለም ልኮታልና ፍቅርም እንደዚህ ነው እግዚአብሔር እርሱ ራሱ እንደወደደን ስለኃጢአታችንም ማስተስረያ ይሆን ዘንድ ልጁን እንደላከ እንጂ እኛ እግዚአብሔርን እንደወደድነው አይደለም።" (1ዮሐ 4፥10) በማለት ሐዋርያው እንደተናገረ።

6. ***አስቀድሞ ወደደን፤***

"እርሱ አስቀድሞ ወዶናልና እኛም ደግሞ እንወደዋለን።" (1ዮሐ 4፥19) ተብሎ እንደተጻፈ።



7. ***ኃጢአተኞች ሳለን ወደደን፤***

"ነገር ግን ገና ኃጢአተኞች ሳለን ክርስቶስ ስለ እኛ ሞቶአልና እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን የራሱን ፍቅር ያስረዳል።" (ሮሜ 5፥8) ተብሏልና።

8. ***ጠላቶቹ ሳለን ወደደን፤***

"ጠላቶቹ ሳለን በልጁ ሞት ታረቀን" (ሮሜ 5፥10, ያዕ 4፥4, ሮሜ 8፥43, 1ዮሐ 2፥15) በማለት መንፈስ ቅዱስ በልሳነ ጳውሎስ እንደተናገረ።

***አንባቢ ሆይ!*** ይህን ፍቅር አትግፋው በሰዎች እንደበት ሊተረጎም ለማይችለው ለእግዚአብሔር ፍቅር ተሸነፍ ዛሬም ኃጢአተኛ ሳለህ ይወድሃልና ንሥሐ በመግባት ፍቅሩን ተቀበለው። በመስቀል ላይ የዋለው የኢየሱስ ክርስቶስ ሕማም፣ ሞት፣ ጸዋትወ መከራ ሁሉ የአብ ፍቅር የተገለጸባቸው መንገዶች መሆናቸውን ልብ በል በመሆኑም ኃጢአት እንዳትሠራ ፍቅሩ እስኪያስገድድህ ድረስ አንተም አምላክህን በፍጹም ልብህ ውደደው።

**ጥያቄዎች**

1. አብ ማን ነው?
2. ወላዲ አስራፂ ፈናዊ ለባዊ አለባዊ በመባል የሚጠራው መለኮታዊ አካል ማን ነው?
3. ወልድን የወለደ መንፈስ ቅዱስን ያሠረፀ ማን ነው?
4. አብ በመለኮታዊ ቃሉ ምን ምን ፈጠረ?
5. አብን በባሕርዩ የሚያውቀው ማን ነው?
6. የአብ ስጦታ ምንድን ነው?
7. የአብ ፍቅር እንዴት ያለ ነው?



መምህር ልዑለ ቃል.